መዝሙር በእንተ ልደቱ ወጥምቀቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ

በወንጌሉ

በወንጌሉ ያመናችሁ /፪/

እንኳን ለብርሐነ ጥምቀቱ አደረሳችሁ /፪/

ልዑል እግዚአብሔር

ልዑል እግዚአብሔር/2/ ምስጋና ይገባሃል/2/

ለዚች ዕለት ለዚች ሰዓት በሰላም

በጤና አደረስከን

ይትባረክ እግዚአብሔ

ይትባረክ እግዚአብሔር አምላኮሙ ለአበዊነ/፪/

ዘገብረ ዐቢየ ወመንክረ

ዘገብረ ዐቢየ /፪/እግዚአብሔር /፬/

ትርጉም- ድንቅና ታላቅ ነገርን ያደረገ የአባቶቻችን አምላክ እግዚአብሔር ይመስገን፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ

ኢየሱስ ክርስቶስ ይወደናል ይጠብቀናል/፪/

በጥምቀቱ ልጅነት ሰጥቶናል/፬/ ኸኸ

እሳተ ጽርሑ

እሳተ ጽርሑ ማየ ጠፈሩ /፪/

ደመና መንኩራኩሩ ለመድኃኔ ዓለም /፬/

ትርጉም፡- ለመድኃኔ ዓለም እሳት አዳራሹ ደመናም መመላለሻው ነው፡፡

ተቀደሰት ዓለም

ተቀደሰት ዓለም በእንተ ጥምቀቱ /፪/

ተቀደሰት ዓለም/፪/ኢትዮጵያ

ተወልደ እምድንግል ሠያሜ ካህናት ወረደ

ክርስቶስ አክሊለ ሰማዕት/፪/

ትርጉም፡- የካህናት ሿምያቸው የሰማዕታት አክሊላቸው ክርስቶስ

ከድንግል ማርያም ተወለደ፡፡ በልደቱም ዓለም/ኢትዮጵያ/ ተቀደሰች፡፡

በጐለ እንስሳ

በጐለ እንስሳ /፬/

በጐለ እንስሳ ተወልደ አማኑኤል/፬/

በእንስሳት በረት/፬/

በእንስሳት በረት ተወለደ አማኑኤል/፬/

<u>*አጽነነ ሰማያተ*</u>

አጽነነ ሰማያተ ወወረደ እግዚአብሔር /፪/

እምድንግል ቃል ሥጋ ዚአነ ለብሰ ወኀብሩ ትስብእት ወመለኮት /፪/

ትርጉም፡- እግዚአብሔር በትህትና ራሱን ዝቅ በማድረግ

ከሰማይ ወረደ ከድንግልም ሥጋችንን ለበሰ መለኮትና ሰውም/ሥጋም/ አንድ ሆኑ፡፡

<u>*አንፈርአፁ*</u>

አንፈርአፁ ሰብአ ሰገል ረኪቦሙ <u>ሕፃነ</u> /፪/

ዘተወልደ ለነ /፬/ ሕፃን ዘተወልደ ለነ /፪/

ትርጉም፡- ለእኛ ብሎ የተወለደውን ሕፃኑን አግኝተው

ሰብአ ሰገል በደስታ ዘለሉ/ሰገዱ/፡፡

<u>*በዮርዳኖስ ተጠምቀ*</u>

በዮርዳኖስ ተጠምቀ /፪/ በሠላሳ ክረምት /፪/

ከመ ይስዓር መርገማ ለሔዋን <u>ዲበ</u> /፪/ ዕፀ መስቀል ተሰቅለ/፪/

ትርጉም፡- በሠላሳ ዘመኑ በዮርዳኖስ ተጠመቀ ሔዋንንም

መርገም ይደመስስ ዘንድ በመስቀል ላይ ተሰቀለ፡፡

<u>*ርዕዩከ ማያት*</u>

ርዕዩከ ማያት እግዚኦ ርዕዩከ ማያት ወፈርሁ/፪/

ደንገጹ ቀላያተ ማያት ወደምጸ ማያቲሆሙ /፬

አቤቱ ውኆች አዩህ ውኆችም አይተው ፈሩህ /፪/

ጥልቆችም ተነዋወጡ ውኆችም ጮኹ/፬/

<u>*ልደቶ ጥም ቀቶ*</u>

ልደቶ ጥምቀቶ አስተርእዮቶ ለመድኃኒነ /፪/

እለ ቀደሙ ነ/፫/መሃሩነ እለ ቀደሙ ነ/፪/

ትርጉም፡-የቀደሙ አባቶቻችን የጌታችንን

ልደቱን፣ጥምቀቱን መታየቱን/መገለጡን/ አስተማሩን፡፡

<u>*ተጠምቀ ሰማያዊ*</u>

ተጠምቀ ሰማያዊ/፪/

በእደ መሬታዊ/፪/

የአምላኮች አምላክ የነገሥታት ንጉሥ/፪/

የዓለም ሁሉ ፈጣሪ የሥጋና የነፍስ

አዝ...

ከባርነት አውጥቶ ነጻነትን ሊሰጠን/፪/
ሐዘናችን አጥፍቶ ሰላምን ሊመግበን

አዝ...

ጠላታችን አፈረ አምላካችን ከበረ/፪/
ስለ ልጁ መጠመቅ እግዚአብሔር መሰከረ

አዝ...

በአንድነት እናቅርብ ለአምላክ ምስጋና/፪/
እልል እልል እንበል ነጻ ወጥተናልና

አዝ...

ጥቂት በጥቂት አደገ በዮርዳኖስ ተጠመቀ/፪/

በዮርዳኖስ /፬/ ተጠመቀ በቅዱስ ዮሐንስ/፪/

<u>በበህቀ ልህቀ</u>

በበህቀ ልህቀ /፪/

በሠላሳ ክረምት በዮርዳኖስ ተጠምቀ /፪/

ጥቂት በጥቂት አደገ /፪/

በሠላሳ ዘመን በዮርዳኖስ ተጠመቀ /፪/

<u>ጥምቀተ ባሕር</u>

ጥምቀተ ባሕር ዮርዳኖስ ነያ

ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ

ጌታችን ሲጠመቅ ባሕር ምን አለች
አልችለውም ብላ ወደ ኋላ ሸሸች
ብርሃን መለኮት በወንዙ ሲመላ
ዮርዳኖስ ሸሸ ሄደ ወደ ኋላ

አብ በመጣ ጊዜ ደመናውን ጭኖ

መንፈስ ቅዱስ ታየ በርግብ አምሳል ሆኖ

ለልጁ ምልክት ሊሰጥ ፈለገና

ቃሉን ተናገረ ሆኖ በደመና

ጌታችን ሲጠመቅ በሠላሳ /፴/ ዓመቱ
ባሕር ኮበለለች ግዑዟ ፍጥረት
ሰማይ ተከፈተ ሆነልን ፀዓዳ
ምሥጢረ ሥላሴ ታወቀ ተረዳ

እልል በይ ዮርዳኖስ የጥምቀት መገኛ

የህይወት መሰላል ድኅነታችን ለኛ

ቀላያት አብርሕት ብዙ ውኖች እያሉ

እንደምን ተመረጥሽ ዮርዳኖስ ከሁሉ

እሰይ እሰይ

እሰይ እሰይተወለደ

እሰይ እሰይ ተጠመቀ

ከሰማየ ሰማይ ወረደ

ከድንግል ማርያም ተወለደ

እርሡ ባይወለድ እሰይ እሰይ

ቸሩ አምላካችን ....

እርሡ ባይጠመቅ ....

መድኃኒታችን ....

መች ትገኝ ነበረ ....

ገነት ርስታችን.......................

ብርሃን ወጣላቸው እሰይ እሰይ

ለእውነት ወገኖች.......................

በጨለማ ጉዞ ....

እንዲያ ሲሰለቹ ....

እንደ ጠል ወረደ እሰይ እሰይ

ከሰማይ ወደኛ ....

ወገኖቹን ሊያድን ....

ከከፉ ቁራኛ.......................

እግዚአብሔር አብ ላከ እሰይ እሰይ

አንድያ ልጁን ....

እርሡ ወድዷልና.......................

እንዲሁ አለሙን ....

*<u>ዮሐን*ስኒ</u>*

ዮሐንስኒ ሀሎ ያጠምቅ /፪/

በሄኖን በቅሩብ ሳሌም/፬/

ትርጉም፤ ዮሐንስ በኢየሩሳሌም አቅራቢያ በዮርዳኖስ ያጠምቅ ነበር

<u>ምድርኒ</u>

ምድርኒ ርእየቶ ወአእኮተቶ/፪/

ባሕርኒ ሰገደት ሎቱ /፬/

ትርጉም ምድርም አየችው አመሰገነችው ባሕርም ሰገደችለት

<u>ወወሊደት</u>

ወወሊደት ወልደ ዘበኩራ /፪/

መንጦላዕት ደመና ሰወራ /፬/

ትርጉም፤ የበኩር ልጇን ወለደች የደመና መጋረጃ ጋረዳት

<u>ጥምቀትከ</u>

ጥምቀትከ ይኩነነ ቤዛ /፪/

ይኩነነ ቤዛ / ፫/ ጥምቀትከ ይኩነነ ቤዛ /፪/

<u>ኀዲጎ ተሰዓ</u>

ኀዲጎ ተሰዓ ኀዲጎ ተሰዓ ኀዲጎ ተሰዓ /፪/

ወተሰዓተ ወተሰዓተ ተሰዓተ ነገደ /፪/

ትርጉም ..፺፱ኙን ነገደ መላዕክት ትቶ በባሕር መካከል ቆመ

<u>ኧኸ ኀዲጎ</u>

ኧኸ ኀዲጎ ተሰዓ ኧኸ ወተሰዓተ ነገደ /፪/

ኧኸ ማዕከለ ባሕር ቆመ ማዕከለ ባሕር /፪/

ኧኸ ፺፱ኙን ኧኸ መላዕክት ትቶ /፪/

ሽኽ በባሕር መካከል ቆመ በባሕር መካከል /፪/

<u>ሰላማዊ ብእሲሁ</u>

ሰላማዊ ብእሲሁ ቅዱሳት እደዊሁ /፪/

እለ አጥመቃሁ /፬ /ለመድኃኔዓለም /፪/

ትርጉም ፤ መድኃኔዓለምን ያጠመቁ እጆቹ የተመሰገኑ ናቸው

<u>ሰላም ለከ</u>

ሰላም ለከ ኦ ፈለገ ዮርዳኖስ ዘተቀደስከ በርደተ መንፈስ ቅዱስ /፪/

ሀየ ንሰግድ ኩልነ ኀበ ተጠምቀ እግዚእነ /፪/

ትርጉም ፤ በመንፈስ ቅዱስ መውረድ የተቀደስከ ዮርዳኖስ ወንዝ ሆይ ሰላም እልሃለው በዚህ ጌታችን በተጠመቀበት እኛ ሁላችን እንሰግዳልን

<u>ቅዱስ እግዚአብሔር</u>

ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ሀያል ቅዱስ ሀያው ዘኢይመውት /፪/

ዘተወልደ እማርያም ወተጠምቀ በዮርዳኖስ ተሥኀለነ እግዚኦ /፪/

ትርጉም፤ቅዱስ እግዚአብሔር ቅዱስ ሀያል ቅዱስ ሀያው የማይሞት ከእመቤታችን የተወለደ በዮርዳኖስ የተጠመቀ አቤቱ ይቅር በለን

<u>ቆመ</u>

ቆመ ማዕከለ ባሕር ገብዓ /፪/

ወወፅዓ በሰላም/፫/

ትርጉም ፤ሰው ሆኖ በዮርዳኖስ ተጠመቀ በባሕር መካከል ቆመ በሰላም ወጣ

<u>ይቤሎ ኢየሱስ</u>

ይቤሎ ኢየሱስ ለዮሐንስ አጥምቀኒ በማይ ከመ ይትቀደስ ማይ በማይተበሰማይ

አጥመቆ ዮሐንስ ለኢየሱስ በፈለገ ዮርዳኖስ

ትርጉም ፤ኢያሱስ ዮሐንስን አለው በሰማይ መባረክ ውሀ ይቀደስ ዘንድ በውሀ አጥምቀኝ አለው ዮሐንስም ኢየሱስን አጠመቀው

እንዲሆነን ቤዛ

እምሰማያት ወረደ ወእም ማርያም ተወልደ ተወልደ/2/
ከመይኩን ቤዛ/2/ለኲሉ ፃለም ወለብሰ ሥጋ ማርያም/2/
ከሰማያት ወረደ ከድንግል ማርያም ተወለደ/2/

እንዲሆነን ቤዛ/2/ለዓለሙ ሁሉ ለበሰ የማርያምን ሥጋ/2/

ለዘተወልደ እምቅድስት

ለዘተወልደ እምቅድስት ድንግል ምንተንብሎ ናስተማስሎ ለመድኃኒነ

አርዌ ገዳምኑ አንበሳ ወሚመ/2/ ከራድዮን

ትርጉም፣ከእመቤታችን የተወለደውን ምን
ብለን እንጠራዋለን፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ

ክርስቶስን በምን እንመስለዋለን በዱር

አንበሳ ነው ወይስ ከራድዮን በሚባል ወፍ ነው::

ሖረ ኢየሱስ

ሖረ ኢየሱስ/4/

እምገሊላ/2/ ኀበ ዮርዳኖስ

ፈለገዮርዳኖስ/2/ ከመያጥምቆ

ትርጉም፣ ኢየሱስ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ
ወረደ በዮርዳኖስ ወንዝ ለመጠመቅ

ወረደ ወልድ

ወረደ ወልድ /6/

እምሰማያት ውስተ ምጥማቃት/2/

ትርጉም፣ ወልድ ክርስቶስ ከሰማያት
ወደ ወንዞች ወረደ

ውስተ ማኅጸነ ድንግል

ውስተ ማኅጸነ ድንግል ኀደረማኅፀነ ድንግል

ሰማይ ወምድር ዘኢያገምሮ

ሰማይ ወምድር በማይ ተጠመቀ

ትርጉም፣ ሰማይና ምድር የማይችሉት
አምላክ በእመቤታችን ማኅጸን አደረ በውሃ ተጠመቀ

መጽዐ ቃል

መጽዐ ቃል እም ደመና ዘይብል/2/

ዝንቱ ውእቱ ወልድየ ዘአፈቅር/4/

መጣ ቃል ከደመና እንዲህ የሚል/2/

የምወደው የማፈቅረው ልጄ ይህ ነው/4/

የዓለምን በደል

የዓለምን በደል የሰውን ግፍ አይቶ

ዘጠና ዘጠኙን መላእክቱን ትቶ

ጽድቅን ለመፈጸም በደልን አጥፍቶ

የሰላሙ መሪ የሰላሙ ዳኛ

አምላክ ተወለደ ተጠመቀ ለእኛ

የሰማዮች ሰማይ የማይችለው ንጉሥ

ተወልዶ ሲጠመቅ እኛን ለመቀደስ

ተራሮች ደንግጠው ዘለሉ እንደፈረስ

አዝ

ባሕር ተጨነቀች ጠበባት መሬቱ

ዮርዳኖስም ሸሸ አልቆመም ከፊቱ

እንደተናገረው ዳዊት በትንቢቱ

አዝ

ልጁ በዮርዳኖስ ጽድቅን ሲመሠርት

መጣ በደመና ሰማያዊው አባት

እየመሰከረ የልጁን ጌትነት

አዝ

እንደምናነበው በወንጌል ተጽፎ

መንፈስ ቅዱስ ታየ በራሱ ላይ አርፎ

በርግብ ምሳሌ ክንፉን አሰይፎ

አዝ

ባሕር ስትጨነቅ ተራራ ሲጨፍር

ሰማዩ ሲከፈት ደመና ሲናገር

ዓለም በዛሬው ቀን አየች ይህን ምሥጢር

አዝ

አማን በአማን

አማን በአማን አማን በአማን/2/

መንክር ስብሐተ ጥምቀቱ/4/

እውነት ነው በእውነት /4/

ድንቅ ነው የጌታ ጥምቀት/4/

እንዘ ሕፃን

እንዘ ሕፃን ልህቀ በዮርዳኖስ ተጠምቀ/2/

በዮርዳኖስ /2/ **ዮርዳኖስ**/2/**ተጠምቀ በዮሐንስ**/2/

<u>ትርጉም</u>፣ሕፃን ሆኖ ጥቂት በጥቂቱ አደገ

በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ

በእደ ዮሐንስ

በእደ ዮሐንስ ተጠምቀ ኢየሱስ ናዝራዊ/2/

ሰማያዊ/5/ **ኢየሱስ ናዝራዊ** /2/

<u>ትርጉም</u>፡– ሰማያዊው የናዝሬቱ ኢየሱስ
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ

ተጠምቀ ሰማያዊ

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ/2/

ተጠምቀ ሰማያዊ በዕደ መሬታዊ/4/

ሃሌ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሃሌ ሉያ ሃሌ ሉያ/2/

አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በልደትህ

አምላክ ሆይ ሕዝቦችህ ዳኑ በጥምቀትህ

<u>ርእይዎ ኖሎት</u>

ዮም ሰማያዊ በጎል ሰከበ ለዘተወልደ እምቅድስት ድንግል /፪/
ርእይዎ ኖሎት /፪/ <u>አእኰትዎ መላእክት</u> /፪/
<u>ትርጉም፡-</u> ዛሬ ከቅድስት ድንግል የተወለደውን
እረኞች አዩት መላእክት አመሰገኑት

<u>ይትፌሥሓ አድባረ ጽዮን</u>

ይትፌሥሓ አድባረ ጽዮን ወይትሐሠያ አዋልደ ኢትዮጵያ /፪/
እስመ ተወልደ ብሑተ ልደት መድኃኔ ዓለም በኢየሩሳሌም መድኃኔ ዓለም /፪/
<u>ትርጉም፡</u> የጽዮን ተራራሮች ይደሰታሉ፤ የኢትዮጵያም ልጆች
ሐሤትን ያደርጋሉ፤
በልደቱ ብቸኛ የሆነ መድኃኔ ዓለም በኢየሩሳሌም ተወልዷልና።

<u>በፍስሐ ወበሰላም</u>

በፍስሐ ወበሰላም /፪/
ወረደ ወልድ /፪/ ውስተ ምጥማቃት /፪/
<u>ትርጉም፡-</u> በደስታና በሰላም እግዚአብሔር ወልድ ወደ መጠመቂያ ወረደ

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

በፍስሐ ወበሰላም እምሰማያት

በአ ስሐ □በሰላም □ምሰማያት /፪/
ወረደ ወልድ ውስተ ምጥማቃት /፬/
ትርጉም፡- በደስታና በሰላም እግዚአብሔር ወልድ ወደ
መጠመቂያ ወረደ

ሥጋ ሰብእ መዋቴ

ሥጋ ሰብእ መዋቴ /፬/
ወገብረ መንጦላዕተ /፰/
ትርጉም፡- የሚሞተውን የሰውን ሥጋ
መሠወሪያው አደረገ (ተዋሐደ)

አስተርአየ ገሀደ

አስተርአየ ገሀደ አስተርዓየ እንዘ ህፃን /፪/
እንዘ ህፃን ልሀቀ/፪/ በዮርዳኖስ ተጠምቀ እንዘ ሕፃን /፪/
ትርጉም፡- በግልጥ ታየ እንደ ህፃናት ቀስ በቀስ አደገ በዮርዳኖስ
ተጠመቀ።

አንሶሰወ

አንሶሰወ /፪/ ወአስተርአየ /፪/
በዮርዳኖስ ኧኸ ተጠምቀ በዮሐንስ /፬/
ትርጉም፡- ተመላለሰ በ□ልፃ ታየ በዩርዳኖስ ወንዝ
በዩሐንስ□እ□ ተ□መቀ።

ነድ ለማየ ባሕር

ነድ ለማየ ባሕር ከበቦ /፪/
ማየ ባሕር ኀበ የሐውር ፀበቦ /፬/
ትርጉም፡- እሳት የባሕሩን ውሃ ከበበው ባሕሩም የሚሄድበት
ጨነቀው።

ክርስቶስ ተወልደ */ወለደነ/*

ክርስቶስ ተወልደ እሰይ
ክርስቶስ ተጠምቀ በማይ
ወለደነ ዳግመ እማይ /፪/ ዳግመ /፪/ ወለደነ ዳግመ እማይ
ትርጉም፡- ክርሰቶስ ተወለደ፣ ክርስቶስ ተጠመቀ ዳግም ከውሃ ወለደን

ክርስቶስ ተወልደ */አስተርእዮቱ/*

ክርስቶስ ተወልደ ወተጠምቀ /፪/
አስተርእዮቱ አማን አስተርእዮቱ /፪/
ትርጉም፡- ክርስቶስ ተወለደ ተጠመቀ መገለጡም እውነት ነው።

ግነዩ ለእግዚአብሔር

ግነዩ ለእግዚአብሔር እስመ ኄር /፪/
እስመ ለዓለም ምሕረቱ እስመ ለዓለም /፬/
እናመስግንሽ የአምላክ እናት በዝማሬ /፪/
የዓለም ቤዛ ነውና የማኀፀንሽ ፍሬ /፬/
ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከአንቺ ተወልዶ /፪/
መለኮት ወረደ ዮርዳኖስ እኛን ለመቀደስ /፬/
በዮሐንስ እጅ ተጠመቀ ዕዳችንን ፋቀ /፪/
በቸርነቱ አወቀን ከበደል አራቀን /፬/
በድንግልና የወለድሽው የአንቺ □ነስ /፪/
የድኩማኖች ብርታት ነው የሕሙማን ፈውስ /፬/
ስምሽን የጠራ ዝክርሽንም ያዘከረ /፪/
በመንግሥተ ሰማይ ይኖራል እንደተከበረ /፬/
ብርሃነ መለኮት ያደረብሽ አዳራሽ /፪/
ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ድንግል አንቺ ነሽ /፬/
እመቤታችን እናታችን ማርያም /፪/
የተማ□ነሽ ይኖራል ለዘለዓለም /፬/

ኀዲጎ ተስዓ

ኀዲጎ ተስዓ ወተስዓተ ነገደ /፪/
ማዕከለ ባህር /፪/ ቆመ ማዕከለ ባህር /፪/
ትርጉም፡- ዘጠና ዘጠኙን ነገደ መላእክት ትቶ በባሕር መካከል ቆመ

አጥመቆ በማይ

አጥመቆ በማይ /፯/
ዮሐንስ /፫/ አጥመቆ በማይ
ትርጉም፡- ዮሐንስ መድ□ኒታችንን በውሃ አጠመቀው

መጽአ ቃል

መጽአ ቃል /፪/ እም ደመና ዘይብል /፪/
እምደመና ዘይብል /፫/ ዝንቱ ወልድየ /፪/
ትርጉም፡- ዘጠና ዘጠኙን ነገደ መላእክት ትቶ በባሕር መካከል ቆመ

ዮሐንስኒ ይቤ

ዮሐንስኒ /፪/ ይቤ ዘአጥመቆ በዮርዳኖስ /፪/
ርኢክዎ ወስእንኩ ጠይቆቱ ስእንኩ /፪/
ትርጉም፡- በዮርዳኖስ ጌታን ያጠመቀው ዮሃንስ ቼታዬን አየሁት እርሱን መርምሬ ልደርስበት አልቻልኩም አለ፤፤

ይእዜኒ ለሰላም

□እዜኒ ለሰላም ንትለዋ ለሰላም /፪/
ተጠምቀ ነዋ መድ□ኔ ዓለም መት□ኒነ መት□ኔ ዓለም /፪/

ሰላም ሰላም

ሰላም ሰላም/፪/
እምይእዜሰ ይኩን ሰላም /፬/
ሰላም ሰላም /፪/
ከእንግዲህስ ይሁን ሰላም /፬/

ዘነቢያት ሰበክዎ

ዘነቢያት ሰበክዎ/2/

ወአስተርዓዩ ገሀደ/2/

ትርጉም፡- ነቢያት የሰበኩት በገሀድ /በግልጥ/ታ□፡

አንፈርዓፁ

አንፈርዓፁ ሰብአ ሰገል/2/

አም□ሆሙ አምፅኡ መትምመ

ትርጉም፡- ሰብአ ሰገል ዘለሉ ሰገዱ/፡፡ የሚያስደንቅ እፀ መንሻንም አመጡ፡፡

መጽአ ከመ ይቤዙ ዓለመ

መጽአ ከመ ይቤዙ ዓለመ /2/

የሀበነ ሰላመ ጋዳ ያበውኡ ቁርባነ /2/

ትርጉም፡- ዓለምን ያድን ዘንድ መጣ፡፡ ሰላምንም ይሰጠን

ዘንድ፡፡እፀ መንሻን እንደ ቁርባን ጸስቶባሉ፡፡

መጽአ ወልድ

ሃሌ ሉያ መጽአ ወልድ ውስተ ዓለም ሃሌ ሉያ ውስተ/2/

ወለብሰ ሥጋነ ሰብአ ኮነ በአርአያ ዚአነ

ትርጉም፡- ከዓለም አስቀድሞ የነበረ ዛሬም ያለ ዓለምንም አሳልፎ የሚኖር ወልድ ወደ ዓለም መጣ፡፡ ሥጋችንን ለበሰ፡፡ በእኛ አርአያ ሰ□ኾነ፡፡

ዘድንግል መናሥግተ

ዘድንግል መናሥግተ ኢያርኂ- /2/

ኢያር□ ዘኪሩቤል ኢርክ□ □□ /4/

ትርጉም፡- □እመቤታችንን የድንግልናዋን ማህተም

አልለወጠም (አልፈተም) ኪሩቤልም አሳ□□ም አልመረመረ□ም፡፡

ኢየሱስ ሖረ

ኢየሱስ ሖረ ሀገረ እሴ□/2/

ዮሐንስ አጥመቆ በማይ/2/

ትርጉም፡- ኢየሱስ ወደ እሴ□ ሀቶረ ቴ□ □ሐንስም በ□ሀ አጠመቀ

መትኃኒነ

መትኃኒነ ተጠምቀ ነዋ/2/

□እ□ኒ ለሰላም ንትለ□/2/

ትርጉም፡- መትኃኒችን አነሆ ተ□መቀ አሁንስ እንግዲህስ ሰላምን እንከተላት

□እ□ኒ

□እ□ኒ ለሰላም ንትለ□ ለሰላም/2/

ስመ ተ□ምቀ □ም/2/ መት ኃኔ□ስም/2/

ትርጉም፡- መትኃኔ□ስም □ሬ ተ□ምቋልና አነሆ ሰላምን እንከተላት፡፡

መ□ወ ቃል

መ□ወ ቃል እም□መና □□ብል/2/

□□□ኦ እማ□ ተርኅ□ ሰማ□/2/

ትርጉም፡- ቃል ከደመና መጣ፡፡ ከውኃ□ም እንደሚ□□ ሰማይ ተከፈተ፡፡

አስተርአየ

አስተርአየ ገሀደ /2/

በስቢሰ ሥጋ ኮነነ ዘመደ /2/

ትርጉም፡- በፅልዓ ታ□፡ ሥጋችንን በመልበስ □መት ሆነን፡፡

ነአምን

ነአምን /2/ ክርስቶስሃ ነአምን መድኅነ /2/

ዘዮሐንስ አጥመቀ በዮርዳኖስ ዘዮሐንስ አጥመቀ /2/ በዮርዳኖስ /2/

እናምናለን /2/ መት ኅን □ርስቶስን /2/ እናምናለን □ርስቶስን

ዮሐንስ ያጠመቀውን በዮርዳኖስ ዮሐንስ ያጠመቀውን በዮርዳኖያጠመቀውን/2/

በእንተ ቃና ዘገሊላ

ጥዒሞ አንከረ

ጥዒሞ አንከረ ሊቀ ምርፋቅ/፪/

በረከተ/፪/ ዘአምላክ ገብረ/፪/ ኧኸ

ትርጉም፡- አምላክ ያደረገውን ተዓምር ተመልክቶ /አጣጥሞ/ የሠርግ ቤቱ አለቃ አደነቀ፡፡

እንዘ ስውር

እንዘ ስውር እምኔነ ይእዜሰ ክሡተ ኮነ/፪/
ተአምረ ወመንከረ ገብረ መድኃኒነ በቃና ዘገሊላ
ከብካብ ኮነ ማየ ረሰየ ወይነ/፪/

ትርጉም፡-በእኛ ተሰውሮ የነበረው የጌታ አምላክነት በገሊላ ሠርግ ግልፅ ሆነ፡፡ በአምላክነቱ ኃይል ውሃን ወደ ወይን ሲለውጥ፡፡/የመጀመሪያው ተዓምር/

<u>አንከርዎ ለማይ</u>

አንከርዎ ለማይ አእኰትዎ ለኢየሱስ /፪/

በእንተ ማይ ዘኮነ ወይነ/፬/

ትርጉም፡- ኢየሱስ ውሃን ወደ ወይን በመለወጡ አመሰገኑት ወይን የሆነውን ውሃውንአይተውአደነቁ፡፡

ማየ ወይነ

ማየ ወይነ ረሰየ /፪/

መዓዛ ቃልከ ይትወከፍ ጸሎትየ መዓዛ ቃልከ ይትወከፍ ጸሎትየ/፪/

ቢቃና

ቢቃና ዘገሊላ/፪/

ዘገሊላ ከብካብ ኮነ/፪/

□ እንዘ □ቶብር

እንዘ □ቶብር ተአምረ □መንክረ በ□ስተ አሕ□ብ /2/

ወስማይኒ ረሰዮ ወይነ ሽከ /4/

<u>ትርጉም</u>፡-በአሕዛብ መካከል ድንቅ ተአምርን(ምልክትን)ሲያደርግ □ኃ□ንወይን

<u>መዝሙር ዘዘወትር</u>

<u>ኵሉ ይሰግድ</u>

ኵሉ ይሰግድ <u>ለሥላሴ</u> /፪/ ኵሉ ይሰግድ /፪
ወይትቀነይ ኵሉ ለመንግሥተ ሥላሴ ለሥላሴ ኵሉ ይሰግድ /፪/
<u>ትርጉም፡-</u> ፍጥረት ሁሉ ለሥላሴ ይሰግዳል ለሥላሴ መንግሥት ፍጥረት ሁሉ ይገዛል፡፡

<u>ሰላም ዘአብ</u>

ሃሌ ሉያ /፪/ ሰላም ዘአብ ወፍቅር ዘወልድ ሃይማኖት ዘመንፈስ ቅዱስ /፪/
ይኅድር ማዕከሌክሙ አምላከ ሰላም <u>ሰላም</u> /፪/ የሀሉ ምስሌክሙ
ሃሌ ሉያ /፪/ የአብ ሰላም የወልድ ፍቅር ሃይማኖት የመንፈስ ቅዱስ
ይደር በመካከላችሁ የሰላሙ አምላክ <u>ሰላም</u> /፪/ ከእናንተ ጋር ይሁን /፪/

<u>እምኵሉ ይኄይስ</u>

እምኵሉ ይኄይስ በሥላሴከ ተአምኖ /፪/
በወላዲትከ /፪/ ወበ ወላዲትከ ተማኅንኖ /፪/
ከሁሉም /፪/ ሥላሴን ነው ማመን ማመስገን /፪/

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

ወልድን በወለደች /፪/ ድንግል አማላጃችን በእርስዋ እንማፀን /፪/

ንጉሥ ውእቱ

ንጉሥ ውእቱ ንጉሠ ሠላም /፬/
አምላክነ /፪/ መድኃኔዓለም /፮/
ንግሥት ይእቲ ንግሥተ ሰላም /፬/
ማርያም /፪/ ኪዳነ ምሕረት /፮/

ትርጉም፡- አምላካችን መድኃኔ ዓለም
የእውነትና የሰላም ንጉሥ ነው
የምህረት ቃል ኪዳን ድንግል ማርያም
የሰላም ንግሥት ናት

ተነሡ እንዘምር

ተነሡ እንዘምር/፪/
በአንድነት ሆነን በእልልታ/፪/ ኧኸ /፫/
ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር /፪/
ለኃያሉ ጌታ ለልዑል እግዚአብሔር

አሥፈሪ ነው ያልነው ብዙ ነገር ነበር
ሁሉንም አለፍነው እግዚአብሔር ይመስገን
ሕዝቦች ደስ ይበለን ሕይወታችን ድኗል
ሰይጣን ጠላታችን አፍሮ ተመልሷል

ሰማይ ዙፋንህ ነው ምድር መረገጫህ
በዚህም በዚያም ቢሆን በሁሉም አንተው ነህ
በሄድንበት ሁሉ ትተለናለህ
ከዕንቅፋት ከድንጋይ ትሠውረናለህ

ስለመልካም ሥራህ አለብን ውለታ
ለማይነገረው የማዳን ስጦታ
ተመስገን እንበልህ ከጧት እስከ ማታ
ሌሌ ምንም የለም የምንከፍልህ ጌታ

አምላክ ሆይ ስምህን ብንጠራው ብንጠራው
አልጠገብ አለን ምንኛ ጣፋጭ ነው
አቤት ያንተ ሥራ ያንተ ልግስና
ቢነገር አያልቅም ስምህ ነው ገናና

መልስ እንድናዘጋጅ ቶሎ ሳንጠራ
ሳለ አንደበታችን ምስጋናህን ያውራ
ምስጋና በሰማይ ምስጋና በምድር
እስከ ዘለዓለም ለስምህ እንዘምር

ከክርስቶስ ፍቅር

ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየኝ ማነው/2/

መከራ ችግር ስቃይ ወይስ መራቆት ነው/2/

አንፈራም አንሰጋም አንጠራጠርም/2/

እግዚአብሔር ከኛ ጋራ ይኖራል ለዘለዓለም/2/

በትጋት ተራምደን እንግባ በጠዋት/2/

በደሙ መሥርቶ ከሠራልን ቤት/2/

ከቶ የት ይገኛል እንዲህ ያለ ቤት/2/

የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት/2/

የውኃ ግድግዳ የደም መሠረት/2/

ይኸው እዚህ አለ የአማኑኤል ቤት/2/

አድርገህልኛልና

አድርገህልኛልና በቸርነተህ አመሰግንሃለሁ እልል/2/
ለዓለመ ዓለም አማኑኤል እገዝልሃለሁ መድኃኔዓለም/2/
ቀኑ ጨልሞብኝ ዙሪያው ገደል ሆኖ
የችግር አረንቋ ፊቴ ተደቅኖ
ረዳት ያጣሁኝ በመሰለኝ ጊዜ
ፈጽሞ አራቅህልኝ የልቤን ትካዜ
አዝ
አምላኬ ጉልበቴ ኃይሌ መመኪያዬ
ጠላት ማሳፈሪያ የእምነት ጋሻዬ
እንደማትተወኝ አሁን አውቄአለሁ
ካለኝ ነገር ይልቅ በአንተ ታምኛለሁ
አዝ
ጥቂቷን አብዝተህ ለምትመግብ ጌታ
የምመልስልህ ባላገኝ ሥጦታ
በቀንም በሌሊትም ሁሌ ለሚያበራ
መንክር ለባሕርይህ ዕጹብ ለአንተ ሥራ
አዝ
አምላክ ሆይ ምስጋና ለአንተ ይገባሃል
ለምስኪኗ ጎጆ በረከት ሰጥተሃል
ድሃ ነኝ አልልም ሀብቴ አንተ ነህና
ማሰሮዬ ሞልቷል ላይጎድል እንደገና

የኃያላን ኃያል

የኃያላን ኃያል/3/ ልዑል እግዚአብሔር/2/
ተአምራትህ ብዙ በሰማይ/2/ በምድር
ተአምራትህ ብዙ በሰማይ/3/ በምድር

ንሴብሖ

ንሴብሖ/2/ ለአምላከ ዕዝራ/2/
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ
ለምስጋና ቀሰቀስከኝ በእኩለ ሌሊት
በተመስጦ ስለፍቅርህ ልጀምር ማኅሌት
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ
አዝ
ስመለከት ወደ ሰማይ በጨረቃ ብርሃን
አስገረመኝ ከዋክብቱ ሲያወሩ ሥራህን
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ
አዝ
አእዋፉ በማለዳ መዝሙር ሲዘምሩ
በቋንቋቸው የአንተን ክብር በምሥጢር ሲያወሩ
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ
አዝ
ከበሮ ሆይ ጸናጽል ሆይ ለምስጋና ተነስ
በማለዳ ለጌታችን ምስጋና እናድርስ
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ
አዝ
ኑ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን በመንፈስ እንዘምር

እልል እንበል በምስጋና ስለሁሉም ነገር
ንሴብሖ ለአምላከ ዕዝራ
ባርከን
ባርከን/2/ ልጆችህን ባርከን/2

በቅዱስ መንፈስህ አንድ ሐሳብ አድርገን/2/

ባርኪን /2/ልጆችሽን ባርኪን/2/

ድንግል ሆይ በምልጃሽ አንድ ሐሳብ አድርጊን

ድንግል ሆይ በምልጃሽ ከልጅሽ አስታርቂን

ጥሪህን ስንሰማ ወዳንተ እንድንመጣ

በሕግህ ልንኖር ከቤትህ ሳንወጣ

በሕይወት ስንደክም እንዳንጠፋ በዓለም

እርዳን ፈጣሪያችን ቸሩ መድኃኔዓለም

ባርከን...

ከተፈረደብን የባርነት ሕይወት

ከመጣብን መርገም በመብል ምክንያት

ከሲኦል እሥራት እኛ የዳንብሽ

ድንግል ሆይ ምንጊዜም አይለየን ምልጃሽ

ባርኪን...

አንድነት ስናጣ ፍቅር ስትመነምን

በምግባር ስንደክም ሲጐድል እምነታችን

በሥጋችን ፈቃድ ወድቀን እንዳንጠፋ

በምሕረትህ ጐብኘን አንተ ሁነን ተስፋ

ባርከን...

ርኅርኅተ ኅሊና ቅድስት እናታችን

አሳስቢ ሁልጊዜ ስለኃጢአታችን

ሊያድነን ነውና ክርስቶስ መሞቱ

አሥምሪን እአምላክ ድንግል ወላዲቱ

ባርኪን...

<u>የሥላሴን መንበር</u>

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት

ኪሩቤል በደመና ዙፋኑን ይዘውት

ድንግልን ከመሐል ሚካኤልን ከፊት

አ□ስአ መላ□ክት ሲሰፅ0 በአርሃት

እዩት ተመልከቱት □ሰማዩን ትምቀት /2/

የሥላሴን መንበር ቅዱሳን ከበውት

እጸሸበሸቡ □ሰማ□ መላእክት

ካህናተ ሰማይ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ሲሉ

ይህን ልዩ ክብር ሲያዩ የታ□ሉ

በጽድቅ ሥራቸው ደምቀው ይታጸሱ /2/

አዝ . . .

የቅዱሳን ሕብረት የቅዱሳን ሀገር

ሲያወድስ ይኖራል የሥላሴን ክብር

ጽድቅና ርህራሄ የተሞላ ሰማይ

እፅ□አብሔር ያድለን በትንሣኤ እንድናይ /3

<u>ቅ0ስ ቅ0ስ</u>

ቅ0ስ ቅ0ስ ቅ0ስ እፅ□አብሔር /2/

□ብተ□ሕ□/2/ □ዒለስ/2/

<u>ትርጉም</u>፡- በአንድነት ሦስት በሦስትነት አንድ የሚሆን እፅ□አብሔር ምስቶን ጽኑክ ልዩ ነው፡፡

<u>ዘይክል ኵሉ</u>

ዘይክል ኵሉ ወአልቦ ዘይሰአኖ ለእፅ□አብሔር

አምላከ ነዳያን ረዳኤ ምንዱባን

ንሕነ ሀቤከ /2/ ተማኅፀነ

የድሆች አለኝ□ ተስፋ ሳ□ ተስፋ

ሁሉንም የሚችል ደራሽ ስተገፋ

ለእኛም ትረስልን በኃ□አት ሳንጠፋ

አዝ . . . /ናዛዜ □□ናን/

ከገነት ሲባረር አዳም ተሳስቶ

ባለቀሰ ጊዜ ልጅነቱን አጥቶ

ትድናለህ ብለህ ያዳንከው በመስቀል

የቅዱሳን አምላክ አቤቱ ችል አትበል

አዝ . . . /ወተስፋ ቅቡጻን/

ሕ□ብ እስራኤልን □ርዖን ሲገዛቸው

ጭንቅና መከራ እያጸናባቸው

በእነራሔል ልቅሶ ሙሴን ሳ□ላቸው

አዝ . . . /ረዳኤ ምንዱባን/

እኛም ወገኖችህ ወደአንተ እንጮሃለን

ከጭንቅ ከመከራ እንድትታደገን

ቴታ አንተ ነህና ናዛዜ ኅ□ናን

አዝ . . . /ናዛዜ □□ናን/

አዝ . . . /ወተስፋ ቅቡጻን/

<u>□□ምሩ ለስሙ</u>

□□ምሩ ስስሙ /2/ ሀቡ ስኰቴተ ስስብሐቲሁ /2/

በል- ስእፅ□አብሔር ፅሩም ፅብርከ /2/

ስስሙም □ምሩ /2/ ምሥጋናን ስቅርቡ ስጌትነቱ /2/

እፅ□አብሔርን /2/ ሥራህ ድንቅ ነው በሉት /2/

በእንተ ማርያም

በምን በምን እንመስላት

በምን በምን እንመስላት ድንግል ማርያምን
ምሳሌ የላትም/፪/ ክብሯን የሚመጥን /፪/
    የሙሴ ጽላት ነሽ የምሕረት ቃል ኪዳን
    የያዕቆብ መሰላል የአብርሃም ድንኳን
    የብርሃን መውጫ የኖኅ ድንቅ መርከብ
    የመላእክት እህት የሩኀሩኃን ርግብ /፪/
የሰሎሞን አክሊል የአሮን በትር
የዕዝራ መሰንቆ የጌዴዎን ፀምር
ድንግል እመቤት ናት የጻድቃኖች በር
ሆና የተገኘች የአምላክ ማኅደር /፪/
    የቅዱሳን እናት የዓለም ንግሥት
    ችላ ተሸከመች መለኮት እሳት
    ብርሃን ትሁነን ጨለማን ገላልጣ
    አማልዳ ታስምረን ከዚህ ዓለም ጣጣ /፪/
ከማር ይጣፈጣል የድንግል መዓዛ
አምላክን አቀፋለች በሁለት እጇ ይዛ
ዓለሙ ሁሉ የዳነው በልጅሽ ነውና
እናታችን ጽዮን ይድረስሽ ምስጋና /፪/

ትውልድ ሁሉ

ትውልድ ሁሉ ብፅዕናሽን ክብርሽን ሁልጊዜ ያደንቃሉ
መመኪያችን መጠጊያችን ተስፋችን አንቺ ነሽ እያሉ /፪/
ያገኑሻል ያከብሩሻል ፍጥረታት በሙሉ /፬/

በአምሳለ ያፍ

በአምሳለ ያፍ /፪/ ፀአዳ ርግብ ትመስል ማርያም ድንግል /፪/
ይእቲኬ ደመና ቀሊል ማርያም ድንግል እሙ ለእግዚአብሔር /፪/
ትርጉም፦ ድንግል ማርያም እንደ ነጭ ርግብ የወፍ አምሳያ ትመስላለች
ይህቺውም ድንግል ማርያም ፈጣኗ ደመና የእግዚአብሔር እናት ናት

ጽላት ዘሙሴ

ጽላት ዘሙሴ ዕፀ ጳጦስ ዘሲና /፪/
ጸናጽል ዘውስተ ልብሱ ለአሮን ካህን /፪/
ትርጉም፦ የሙሴ ጽላት ጳጦስ የተባለች የሲና ዕፅ
በካህን አሮን ልብስ የነበረች ጸናጽል እርሷ ነች

ዘየሀይድ ዓይነ

ዘ□ሀይድ ዓይነ /፪/ ልበሰ ክበር ለቢሶ ዳዊት /፪/
ቅድመ ታቦተ ሕግ ኀለየ ቅድመ ታቦተ ሕግ /፪/
ትርጉም፦ ዳዊት ዓይን የሚሰውር /የሚያብረቀርቅ/ ልብስ ለብሶ
በታቦተ ሕግ /ታቦተ ጽዮን/ ፊት ዘመረ

<u>ማርያም ደስ ይበልሽ</u>

ማርያም /፫/ ደስ ይበልሽ በገብርኤል ሰላምታ
በአንቺ ስላደረ የዓለም ሁሉ ጌታ /፪/
የአምላክ ቸርነቱ ፈቃዱ ሲሆን
ጨለማው ተገፍፎ ሲመጣ ብርሃን
መድኃኒት ሲመጣ ሰይጣን እንዳፈረ
የዜናው አብሣሪ ገብርኤል ነበረ
አዝ-----------------
ድንግል ተቀምጣ በቤተ መቅደስ
ሐር ወርቅ አስማምታ ስትፈትል ንግሥት
ገብርኤል /፪/ ዜናዊ ሐዲስ
የአምላክን መወለድ ሥጋ በመልበስ
አዝ-----------------
ገብርኤል ሲያበሥራት ድንግል ስትሰማ
በእርሷ ላይ አረፈ የመለኮት ግርማ
እውነተኛ መልአክ መሆኑን ስላየች
ይሁንልኝ ብላ ቃሉን ተቀበለች

<u>ታቦተ ሕጉ</u>

ታቦተ ሕጉ ለእግዚአብሔር በካህናት ህፅርት ወበመንፈስ ቅዱስ ክልልት /፪/
ንጉሥኪ ጽዮን ኢይትመዋዕ ለፀር ወኢየ□ድኃ ለህገር /፪/
የሕግ ጽላቱ ለእ□ዚአብሔር በካህናት የታጠረች በመንፈስ ቅዱስም የተከለለች /፪/
ንጉሥሽ ጽዮን አይሸነፍም ለጠላት ሀገራቱንም አይተዋትም /፪/
<u>ትርጉም፡-</u> 1. ሰሙ፡ ለጽዮን ለእሥራኤል ዘሥጋ
ወርቁ፡ ጽዮን ቤተ-ክርስቲያን ንጉሥሽ ክርስቶስ ስትፈተኚ
ቢያይም መንግሥተ ሰማያትን ከመስጠት አይተውም
2. አማናዊት ጽዮን ማኅደረ መለኮት ድንግል ማርያም ናት

መሠረተ ሕይወት

መሠረተ ሕይወት ማርያም ወጥንተ መድኃኒት ዘእምቀዲሙ/2/
ለወልድኪ/2/ አምሳለ ደሙ/2/
<u>ትርጉም፡</u>–ቅድመ ዓለም የነበረ መድኃኒት ከሚባል የተገኘሽ የህይወት መሠረት
ማርያም አንቺ ነሽ መሠረትነትሽም የልጅሽ የደሙ ምሳሌ ነው፡፡

ጽላት

ጽላት ዘሙሴ ጽላት/2/ ሕግ ወሥርዓት/2/
ሙሴ ከፈጣሪ የተቀበላት
አሥርቱ ትዕዛዛት የተጻፈባት
ጽላት ዘሙሴ ጽላት

ምክሆን ለደናግል

ማርያም ድንግል ምክሆን ለደናግል

ይእቲኬ ቤተ ምስአል ዘአስተአጸቡ ታቀልል

ለኩሉ ፍጥረት ትተነብል በአክናፈ መላእክት ትትኬለል

ይእቲ ተዐቢ እምኪሩቤል ወትፈደፍድ እምሱራፌል

ማርያም ድንግል መመኪያቸው የደናግል እርሷም

እኮ የምልጃ ቤት ናት የሚያስጨንቀውን የምታቀልል

ለፍጥረት ሁሉ ትማልዳለች በመላእክት ክንፎችም ትጋረዳለች እርሷ ትበልጣለች ከኪሩቤል ደግሞም ትልቃለች ከሱራፌል

<u>መሐርኒ ድንግል</u>

መሐርኒ ድንግል ወተሰሃልኒ በበዘመኑ/፪/

ለእመ መሐርከኒ/፫/ አንቲ ዘይኴንነኒ መኑ

ኲናኔ *ሥጋ* ወነፍስ/፫/ ወልድኪ አኮኑ /፪/

ትርጉም- ድንግል ሆይ ማሪኝ በየዘመኑ ተለመኝን አንቺ ከማርሽኝ
የሚፈርድብኝስ ማነው በሥጋና በነፍስ የሚፈርድ ልጅሽ አይደለምን?

<u>ለምኚ ድንግል</u>

ለምኚ ድንግል ለምኚ

ለኀጥአን አይደለም ለፃድቃን

ለምኚ.. ታላቅ ስጦታዬ

...........አዛኝ ርኅሩኅ ነሽ

............የጌታዬ እናት

.... ጸጋን የተሞላሽ

.... የአምላክ ማደርያ

.... ለምነሽ አስምሪኝ

....................አማናዊት ጽዮን

....................ከእኔ አትለይኝ

አዝ

ለምኚ..ሐዘንሽ ሐዘኔ

............ለእኔ ይሁን ድንግል

..............የተንከራተትሽው

............በሀገረ እስራኤል

.... ትዕግስትሽን ሳየው

...........ልቤ ይመሰጣል

.............የሐዘን እንባ ጎርፍ

...........ዐይኔን ይሞላዋል

አዝ

ለምኚ..በቀራንዮ አምባ

..........በዚያ በፍቅር ቦታ

............ከእግረ መስቀሉ ስር

...........ከክርስቶስ ጌታ

.... ለእኛ ተሰጥተሻል

.... እናት እንድትሆኚን

.... ልጆችሽ ነንና

.................ምልጃሽ አይለየን

አዝ

ለምኚ..አንደበቴነን ጌታ

.... ለምስጋና መላው

.... ደስ ይበልሽ ብዬ

.... እኔም ላመስግናት

.... አንደበቴነን ጌታ

.... ለምስጋና መላው

.................ደስ ይበልሽ ብዬ

.... እኔም ላመስግናት

ክነፈ ርግብ

ክነፈ ርግብ በብሩር ዘግቡር ወገበዋቲሃኒ በሐመልማለ ወርቅ /፪/
አንቲ ምስራቅ ወወልድኪ ፀሐየ ጽድቅ አማን በአማን/፫/ /፪/
ኢየኀልቅ ኪዳንኪ ወላዲተ አምላክ

እንደ ርግብ ክንፍ በብርም እንደ ተሰራች ጎኖችሽም የወርቅ ሐመልማል/፪/
አንቺ ምስራቅ ነሽ ልጅሽም የጽድቅ ፀሐይ ነው እውነት በእውነት/፫/ /፪/
አያልቅም ቃል ኪዳንሽ የአምላክ እናት

የዐቢ ክብራ

የዐቢ ክብራ ለማርያም እምኵሎሙ ቅዱሳን /፪/ /፪/
እስመ ድልወ ኮነት ለተወክፎ ቃለ አብ
ዘይፈርህዎ መላእክት ወየአኵትዎ ትጉሃን በሰማያት /፪/
ማርያም ድንግል ጾረቶ በከርሳ/፪/

ትርጉም፦ የድንግል ማርያም ክብር ከቅዱሳን ክብር ይበልጣል የአብን ቃል ለመቀበል በተገባ ተገኝታለችና መላእክት የሚፈሩትን ትጉሆች በሰማያት የሚያመሰግኑትን ድንግል ማርያም በማኅፀኗ ተሸከመችው፡፡

አንቺ የወይን ሐረግ

አንቺ የወይን ሐረግ ድንግል ልምላሜሽ የበዛ/2/

ምግብ ሆኖ /2/ ተሰጠን ፍሬሽ ለኛ ቤ□/2/

ባንቺ ሰማይነት የወጣው ፀሐይ/2/

ብርሃን ነው /2/ ለፃድቃን ለሙም አደናይ/2/

ፊደል ትመስያለሽ ድንግል ወንጌል ትወልጃለሽ/2/

ለመላእክት /2/ የማይቻል ነበልባሉን የቻልሽ/2/ እኮ

የመሶብ ምሳሌ ድንግል የኵከብ መገኛ/2/

በሥጋችን በነፍሳችን እንዳንራብ አንቺ አለሽን ለኛ/2/

ምንተኑ አአስየኪ

ምንተኑ አአስየኪ እሴተ

በእንተ ኵሉ □ቶበርኪ ሊተ/2/

የቅዱሳን ተስፋ የትንቢት ምዕራፍ

የስደተኛች ስንቅ የምሕረት ደጃፍ

የፍጥረት መመኪያ ምክንያተ ድኂን

ለእኔም ለመንገዴ ስለሆንሽኝ ብርሃን

የዓለም ኑሮ ማርኮኝ ልቤ ሲዋልል

በፈተናው ብዛት በሕይወት ስዝል

ለሥጋዬ ፈቃድ ከቶ ስላልተውሽኝ

ለነፍሴም ሰላምን ስላስገኘሽልኝ

በኃ□አት መ□ስቀሴን ትካሜን ሳታ□

በሐዘን በችግሬ ከእኔ ሳትለ□

ከመከራ አዘቅት በአንቺ ስለወጣሁ

ለብ□ □ለታሽ ምን እከፍልሻለሁ

የአዝማቹ ትርጉም፡ ስላደረግሽልኝ ሁሉ ምን □ከፍልሻለሁ ማለት ነው፡፡

1. **ሰአሊ ለነ**

ሰአሊ ለነ ማርያም ሰአሊ ለነ /2/

ወልድኪ ይምሐረነ ወመዋርስቲሁ ይረስየነ መትኃኔ□ስም /2/

ለምኝልን ድንግል ማርያም ለምኝልን /2/

ልፀ ሽ □ቅር እንዲለን □መንግሥቱም □ራሾች እንዲጸ□ርገን /2/

በእንተ ቅዱሳን መላዕክት

ክብሮሙ ለመላእክት/ ሙራደ ቃል/

ክብሮሙ ለመላእክት ከመ መንኩራኩር ወረደ መልአከ እግዚአብሔር/፪/

ኀበ ማርያም ድንግል ለተናግሮ ለሙሴ በኀበ ዕፀ ጳጦስ/፪/

እንዳንተ ማንም የለም ከቶ የሚመስልህ

አምላክ ሆይ ድንቅ ነው ሥራህ

አዳምን ከነ ልጆቹ ልታድን በገባኸው ቃል

አዳንከው እንደ ቃልህ ተወልደህ ከድንግል

ቅድመ ዓለም የነበርህ ያለህና የምትኖር

ልዑለ ባሕርይ ሕያው እግዚአብሔር

ብስራታዊ መልአክ ቅዱስ ገብርኤልን

ላከው የመምጣትህን ዜና እንዲሰብከልን

ሙሴን የተናገረው በእሳቱ ነበልባል

የመላእክት ፍቅር የሰማዕታት አክሊል

ከሰማያት ወረደህ እንደ መንኩራኩር

ዓለምን ለማዳን ከድንግል ተወልደህ በረቀቀ ምሥጢር

በፍጡራን ኅሊና የማትመረመር

ድንቅ ነው በእውነት የልደትህ ነገር

የአዳም ተስፋ ነህ የድኅነት መገኛ

ክርስቶስ ሥጋችንን ለብሰህ ተወለድክልን ለኛ

<u>□እቱ ሚካኤል</u>

□እቱ ሚካኤል □እቱ መልአከ ኃ□ል /2/ ልዑል □እቱ ልዑለ መንበር

ይስአል ለነ ይስአል ለኢትዮጵያ ረዳኤ ይኩና አመ ምንዳቤ /2/

<u>ትርጉም</u>፡- የሰላም መልአክ ኃ□ልን □ሚጸ□ረፅ መልአክ ሚካኤል መንበሩ ልዑል ነው፡፡ ለእኛ □ለምንልን፡፡ ለኢትዮጵያም □ለምንሳት፡፡ በመከራ ቲ□ም ረዳት □ሁናት፡፡

<u>አንስዕ ኃ□ለከ</u>

አንስዕ □□ለከ ወ፮አ አድኅነነ /2/

ሚካኤል /2/ ርድአነ

ሚካኤል /2/ በጸሎትከ ተማኅፀነ /2/

ኃይልህን አንሳ መጥተህ አድነን /2/

ሚካኤል /2/ ተራዳ}ን

ሚካኤል /2/ በጸሎትህ ስምንማፀን /2

<u>ከመትባርከነ</u>

ከመ ትባርከነ በመስቀልከ ዘወርቅ/2/

ተዋነይ በጽድቅ/4/ ገብርኤል ሐመልማለ □ርቅ/2/

<u>ትርጉም</u>፡- በክቡር መስቀልህ ትባርከን ዘንድ ገብርኤል

ሆ□ በእ□ነት በረድኤት ተመሳስስ፡፡

<u>ሚካኤል</u>

ሚካኤል እመላእክት መኑ ከማከ ልዑል/2/

አስተምሕር ለነ ሰአልናከ

በአሠርቱ ወአርባዕቱ ትንብልናከ /2/

ዐይኑ ዘርግብ ልብሱ ዘመብረቅ

ሐመልማለ ወርቅ /2/

ይሰግድ በብረኪሁ እስከ

ይመጽእ ሥርየት ለኃጥአን /2/

ሚካኤል እመላእክት መኑ ከማከ ክቡር

ሚካኤል እመላእክት መኑ ከማከ ልዑል

መኑ ከማከ ክቡር መኑ ከማከ ልዑል/2/

ሚካኤል ከመላእክት እንዳንተ ያለ ማነው የአምላክ ባለሟል/2/

ለምንልን/፪/ ለመንህ

በአሥራ አራቱ የጸሎት ሥርዓትህ /2/

ዐይኑ የርግብ ነው የወርቅ ሐመልማል

ልብሱ የመብረቅ ነው/2/

ይሰግዳል በጉልበቶቹ ለኃጥአን

እስኪሰጥ የአምላክ ሥርየቱ/2/

ሚካኤል ከመላእክት እንዳንተ ያለ ማነው የአምላክ ባለሟል/2/

እንዳንተ ያለ ማን አለ/2/

ለረዲኦትየ ነዓ

ለረዲኦትየ ነዓ ሰፈሐከ ክንፈ /፪/

ረዳኤ ምንዱባን /፪/ ሚካኤል በከመ ታለምድ ዘልፈ /፪/

ትርጉም፣ የተቸገሩትን የተጨነቁትን ዘወትር እንደምትረዳቸው ሁሉ ሚካኤል እኔንም ለመርዳት ክንፍህን ዘርግተህ ፈጥነህ ድረስልኝ

ውእቱ ሊቆሙ

ውእቱ ሊቆሙ ለመላእክት ወመልአኮሙ ስሙ ሚካኤል

ልብሱ ዘመብረቅ ዓይኑ ዘርግብ ሊቀመላእክት/2/

ትርጉም:- የመላእክት አለቃቸው ቅዱስ ሚካኤል ልብሱ የመብረቅ ዓይኑም የርግብ ነው

ልዑል ውእቱ

ልዑል ውእቱ ልዑለ መንበር/4/

ሚካኤል/2/ ልዑለ መንበር/2/

ትርጉም: ከፍ ከፍ ያለነው መቀመጫውምከፍ ከፍ ያለነው ሚካኤል መቀመጫው ከፍ ከፍ ያለነው

ሚካኤል ሊቅ

ሚካኤል ሊቅ ልብሱ ዘመብረቅ/2/

ዓይኑ ዘርግብ ዓይኑ/4/ ሚካኤል ሐመልማለ ወርቅ/2/

<u>ትርጉም</u>:-አለቃ የሆነው ሚካኤል ልብሱ፡መብረቅ ነው ዓይኖቹም የርግብ ዓይን ይመስላሉ ሚካኤል የወርቅ ሐመልማል ነው

ሚካኤል አማልደን

ሚካኤል አማልደን ከአምላካችን/2/

እንዳንጠፋ እንዳንሞት በነፍሳችን/4/

ቀዋምያን ለነፍሳት

ቀዋምያን ለነፍሳት እሙንቱ ሊቃናት

ዑራኤል ወሩፋኤል

ይትፌነው ለሳሕል/2/እም ኀበ ልዑል

ለነፍሳት የቆሙ እነዚህ መላእክት

ዑራኤልና ሩፋኤል

ከልዑል ዘንድ ለይቅርታ/2/ ይላካሉ ከልዑል/2/

አምላከ እሥራኤል

አምላከ እሥራኤል ታማኝ ጌታችን

ለእሥራኤል ለሙሴ የሆንከው መድኅን

ፈርዖን ቢጸና በትዕቢት ቢገን

ለእሥራኤል አርበኛ መረጥከው ሙሴን

አማላጅ ነው ሚካኤል/2/ የአምላክ ባለሟል

ለነሙሴ ለሕዝበ እስራኤል

ፈርዖን እንደገና ልቡ ተጸጽቶ

ቢከተላቸውም ጦሩን አስከትቶ

ይመራቸው ነበር ሚካኤል በፋና

ሌሊቱን በብርሃን ቀኑን በደመና

ሙሴ እንደታዘዘው አነሣ በትሩን

እጆቹን ዘረጋ ከፈለው ባሕሩን

እንደ ግንብ ቆመ ባሕረ ኤርትራ

በደረቅ አለፉ እሥራኤል በተራ

መልአከ ሰላምነ

መልአከ ሰላምነ ሊቀመላእክት ዑራኤል/2/

ሰአል ወጸልይ በእንቲአነ አዕርግ ጸሎተነ ቅድመ መንበሩ ለመድኃኔዓለም

ትርጉም:–የሰላም መልአክ ቅዱስ ዑራኤል ስለ እኛ ለምንልን ጸሎታችንንምበመድኃኔዓለም ፊት አሳርግልን

በእንተ ቅዱሳን ፃድቃን

ጥምቀተ አምጽአ

ጥምቀተ አምጽአ ሐፅወ ንግሥት ለእሊአሁ
እምነበ ፊሊጶስ ድኅረ ተጠምቀ ለሊሁ
ሰላማ አቡነ አምጽአ ለነ በዕድሜሁ ለመድኃኒነ
ምስጢረ ደሙ ወሥጋሁ
ትርጉም፡- *የንግሥቲቱ ጃንደረባ በፊልጶስ ዘንድ ራሱ ከተጠመቀ*
በኋላ ጥምቀትን አመጣልን፤ አባታችን አቡነ ሰላማም በዘመኑ የመድኃኒታችንን የደሙንና የሥጋውን ምስጢር አመጣልን፡፡

በመንፈስ የሐውር

በመንፈስ የሐውር እም ኃይል ውስተ ኃይል /፪/
ካህን /፪/ ወነቢይ /፪/ ዮሐንስ መጥምቅ /፪/
ትርጉም፡- *ከኃይል ወደ ኃይል በመንፈስ ሄደ*
ካህንና ነቢይ ዮሐንስ መጥምቅ

ያሬድ ሐዋርያ

ያሬድ ሐዋርያ/፫/

ዘአብርሃ ለኢትዮጵያ/፪/

ትርጉም- ያሬድ ሐዋርያ ለኢትዮጵያ አበራ፡፡

ይቤለኪ ያሬድ

ይቤለኪ ያሬድ በሃሌ ሉያ/፪/

ብሔረ አግዐዚ ቅድስት ኢትዮጵያ/፪/

ትርጉም- ያሬድ በመዝሙር የነጻነት ሀገር ቅድስት ኢትዮጵያ ናት ይልሻል፡፡

ሰባኬ ወንጌል

ሰባኬ ወንጌል መጋቤ ሃይማኖት ለቤተ ክርስቲያን ዘይደምፅ /፪/

ቀርን ነባቤ ለቤተ ክርስቲያን

ያሬድ ፀሐያ ለኢትዮጵያ ዓምደ ብርሃን ለቤተ ክርስቲያን መልአክ ዘበምድር/፪/ መልአክ/፪/

ትርጉም፡- ቅዱስ ያሬድ ሰባኬ ወንጌል መጋቤ ሃይማኖት ለቤተ ክርስቲያንም የሚመሰክር መለከት ነው፡፡ የኢትዮጵያ ፀሐይ የብርሃንም ምሰሶ በምድር ላይ ያለ መልአክ ነው፡፡

በመንፈስ የሐውር

በመንፈስ ዮሐውር እምኃ□ል □ስተ ኃ□ል/2/

ካህን/2/ ወነቢይ ካህን ወነቢይ ዮሐንስ መጥምቅ/2/

<u>ትርጉም</u>፡-ካህንና ነቢይ የሆነው መጥምቁ ዮሐንስ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ከኃ□ል □□ ኃ□ል □ጻ□ል፡፡ በ□□ መንፈሳዊ ሀብት ክስትዕስት □ፄ መረጸ□ች □ሄቴል፡፡

2. <u>ዜናኩ ጽድቀከ</u>

ዜናኩ ጽድቀከ ወነገርኩ አድኅኖተከ

ከሠትኩ ቃሳቲከ ለሕዝብከ ኢትዮጵያ /2/

በጸጋሁ ለመንፈስ ቅዱ፟ስ ወመሀርክዎሙ አነ ይቤ ያሬድ ካህን /2/

ጽድቅህን ነገርኩ አዳኝነትህን አስተማርኩቃሳትህን ለኢትዮጵያ ሕዝብህ ገለጥኩ

እኔም በመንፈስ ቅዐ ስ ና□ አስተማርኩአቸው አለ ያሬድ ካህን /2/

<u>ይትፌሥሑ ጻድቃን</u>

ይትፌሥሑ ጻድቃን የዋሃን ውሉደ ብርሃን/፪/
በትፍሥሕት ዔሉ ውስተ አድባር/፬/ ኸኸ

ትርጉም፡- የብርሃን ልጆች ጻድቃን ደስ ይሰኛሉ በደስታም ከተራራ ወደ ተራራ ዞሩ/ገዳም ገቡ/፡፡

<u>ዘረከቡኪ ጻድቃን</u>

ዘረከቡኪ ጻድቃን ማርያም ድንግል/፬/
መንግሥተ ሰማያት/፪/ ማርያም /፪/

ትርጉም፡- ጻድቃን ያገኙሽ የሰማይ መንግሥት ማርያም አንቺ ነሽ፡፡

<u>ወዐቀቦሙ</u>

ገነተ ትፍሥሕት ኪያሃ አውረሶሙ ወዓቀቦሙ ከመ ብንተ ዓይን ለጻድቃን/፪/
እለ ሎቱ ተቀንዩ በሕይወቶሙ/፬/

ትርጉም፡- ጻድቃንን እነደ ዓይን ብሌን ጠብቃቸው እነርሱንም በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ ተገዝተውለታልና፡፡

<u>ዮሐንስ ከቡር ነቢየ ልዑል</u>

ዮሐንስ ክቡር ነቢየ ልዑል/፪/
ብእሴ ሰላም/፬/ ዘንብረቱ/፪/ ገዳም/፪/ኸኸ

ትርጉም፡- ክቡር ዮሐንስ የእግዚአብሔር ነቢይ
የሰላም ሰው ኑሮው በዱር የሆነ/ሰውነቱን ለገዳም ያዘጋጀ/፡፡

ይቤሎ መንፈስ ቅዱስ

ይቤሎ መንፈስ ቅዱስ ለፊልጶስ ሑር ወትልዎ ለዝንቱ ሠረገላ ዘአፍራስ/፪/
ፊልጶስ መሀሮ ለባኮስ በእንተ ክርስቶስ ወአጥመቆ በማየ ጥምቀት ሐዲስ/፪/
አለው መንፈስ ቅዱስ ፊልጶስን ሂድና ተከተለው ይህንን የአፍራስ ሠረገላ/፪/
ፊልጶስ አስተማረ ለባኮስ ስለ ክርስቶስ አጠመቀውም በማየ ጥምቀት ሐዲስ/፪/

አሰርገዋ

አሰርገዋ ለኢትዮጵያ በስብሐት ወበ ሃሌ ሉያ /፪/

ያሬድ ካህን ጥዑመ ልሳን ለቤተክርስቲያን ፀሐያ /፪/

አሸበረቃት ኢትዮጵያን በምስጋና ወበ ሃሌ ሉያ /፪/

ካህኑ ያሬድ ልሳኑ ጣፋጭ ለቤተ ክርስቲያን ብርሃኗ/፪/

ሰአሉ ለነ

ሰአሉ ለነ ቅዱሳን መላእክት/፪/
ሰአሉ ለነ ጻድቃን ሰማዕት
ኀበ አምላከ ምሕረት ሰአሉ ለነ
ለምኑልን ቅዱሳን መላእክት/፪/
ለምኑልን ጻድቃን ሰማዕታት
ወደ አምላከ ምሕረት ለምኑልን
    አንተ የመረጥከውን ማን ይከሳል
    ያጸደቅከውን ማን ይወቀሳል
    ለሚገባው ክብርን መስጠት
    ታዟልና በመጻሕፍት
    ያከበርካቸውን ባሪያዎችህን /፪/
    እናከብራለን ቅዱሳንህን.
ሁሉ መዳንን እንዲያገኙ
የሚላኩ የሚያግዙ
ሰርክ በፊትህ የሚቆሙ
ጥዑም ቅዳሴህን የሚያሰመ
·በምስጋናቸው የሚያከብሩህን /፪/
እናከብራለን መላእክትህን .
    □ᎋ□ ልሰ□· □□ ዓ ሰ□·
    □ክ□ ቁሩንም ታ□ሰ□·
    በ□አ ር□ታ□· በ□ዐ ሩ
    ሌ□ ለብሰ□· እ□ዞሩ
    በጽናታቸው ያከበሩህን
    እናከብራለን ጻድቃንህን /፪/.
እንደሚታረዱ በጎች ሆነው
አንገታቸውን ለሰይፍ ሰጥተው
ስለ ስምህ □□ተ□ሉ

ከአንበሳ ጋራ እ□ታገሉ
በተጋድሏቸው ያከበሩህን
እናከብራለን ሰማዕታትህን /፪/

ከሕያው ቃልህ □□ቀሱ
መናፍቃንን ድል እየነሱ
በገዛ ደምህ የዋጀሃትን
ቤተ ክርስቲያንን የጠበቋትን
በሕ□□ታቸው ያስደሰቱህን
እናብራለን ቅዱሳህን /፪/

1. ***<u>የሕይወትን መዝገብ</u>***

የሕይወትን መዝገብ ቃሉን ያስነበቡህ
የተዋሕዶ አርበኞች ቀዱሳን ዋናችህ
የድካም ዋጋቸው የእምነታቸው ፍሬ
ያማረ ነውና ምስላቸው ዛሬ
አዝ...
ምሥ□ሩ ምንድነው ድል የማድረጋቸው
ለሰማያዊ ክብር ለአክሊል ያበቃቸው
□ሕ□□ታቸውን መዝገብ ግለጥና አንብበው
መፍትሔ አለውና ገድላቸው የአበው
አዝ...
ትካም ሲበረታ በመንፈስ ስትዝል
ዙሪያህን ሲከብህ የኀጢአት ማዕበል
ጽናት ትዕግስት አጥተህ □ንዳትሰናከል
በጾም ጸሎት በርታ አባቶችን ምሰል
አዝ...
ዓለም ኢያርኮ ቢፈትንህ ሥጋ
□ጸብሎስም ቢያሴር ከመንገድ ሊያርቅህ
ልትወድቅ አትችልም ምን ቢያይል ፈተና
ካሰብክ የጸኑትን የተዋሕዶን ፋና

<u>በእንተ ቤተ ክርስቲያን</u>

2. ***<u>ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ጥበባት</u>***

ቤተ ክርስቲያን ባሕረ ጥበባት /፪/

አትመረመርም /፪/ እጅግ ጥልቅ ናት /፪/

በሥ□ዊ ዓበብ ለማ□ቅ ቢቃ□

□እምነት መነጽሩን ይዞ ስላልመ□ /፪/

አንዳንዱ በክህደት/፪/ ፈጣሪውን አጣ /፪/

እንመሰክራለን ፈጣሪያችን አለ

እንመሰክራለን አማኑኤል አለ /፪/

እንመነው አንካደው አማኑኤል ቸር ነው

እንመሰክራለን ድንግል አማላጅ ናት /፪/

እንመሰክራለን ማርያም አማላጅ ናት

እንመናት አንካዳት የአምላክ □እናት ናት /፪/

<u>በደምህ ዋጅተህ</u>

በደምህ ዋጅተህ ያፀናሃትን
ጠብቅልን ቤተ ክርስቲያንን } /፪/

አዝ...

ጽዮንን ክበቧት ደጆቿንም ዙሩ

ሲል ያመሰገናት ዳዊት በመዝሙሩ/፪/

አዝ...

ወልድ ዋሕድ ብሎ ጴጥሮስ ሲመሰክር

መሠረት ነህ ብለህ ሰጥተኸዋልና ክብር/፪/

አዝ...

እመሠርታለው በአንተ መሠረት

የሲኦል አበጋዝ አይችልም ለማጥፋት/፪/

አዝ...

የቅዱሳን ሀገር የአምላክ ማደሪያ

ምዕራገ ጸሎት የኃጢአት ማስተሰሪያ/፪/

አዝ...

<u>ወደ ቤተ እግዚአብሔር</u>

ወደ ቤተ እግዚአብሔር እንሂድ ሲሉኝ /፪
እንደ ዳዊት እንደ ንጉሡ ተደሰትኩኝ /፪
መላእክት በሰማይ የሚያመሰግኑህ /፪
አምላካችን ፈቃድህ ይሁን እንዘምርልህ /፪
ሞትን አሸንፎ ለተነሳው ጌታ /፪
ዘምሩለት ተቀኙለት በጧት በማታ /፪
በመስቀል ላይ ሳለ ሲወጋ ጎኑን /፪
ውሃና ደም አንድ ላይ ሆኖ ፈሰሰልን /፪
በውሃው ተጠምቀን ደሙን ጠጥተን
መንግሥቱን እንድንወርስ ስላደረገን
ስሙ ይክበር ከፍ ከፍ ይበል የጌታችን
ስሙ ይክበር ከፍ ከፍ ይበል የአምላካችን

<u>እምርኀቅሰ</u>

እምርኀቅሰ ርእ□□ □ተአምእ□ ወአእመሩ ከመ ሀቶሮሙ □እቲ /2/

ገነት ይእቲ ነቅ□ ገነት አዘቅተ ማየ ሕይወት ማኅ□ር ስንጹሐን /2/

ከሩቅ ሆነው አይዋት ተሳሰሟት ሣገራቸውም እንደሆነች አወቁ/2/

ገነት ናት ነቅዓ ገነት የሕይወትምንጭ የንጹሐን ማደርያ /2/

ቤተክርስቲያን አሐቲ

ቤተክርስቲያን አሐቲ አንቀጸ አድኅኖ □እቲ /2/ ደብረ ምሕረት /2/

ትግሁ ባቲ/2/ ሕዝበ ክርስቲያን ሽከ □ነበለ አጽርፃ /2/

ትርጉም፡- ቤተክርስቲያን አንዲት ናት፡፡ የድህነት በርም ናት፡፡ የምሕረት ተራራ ናት፡፡ የክርስቲያን ወገኖች ያስማስ□ቶል (ጸስማቋረዓ) ትጉባት (አገልፅሉባት)፡፡

ንዑ ንስግድ

ንዑ/፪/ ንስግድ ኩልነ/፪/

ማኅደረ ሰላምነ ቤተ ክርስቲያን/ኢትዮጵያ/፪/

ትርጉም፡- ኑ የሰላማችን መገኛ ወደ ሆነች ወደ ቤተ ክርስቲያን ሁላችንም እንስገድ፡፡

ጽንዑ

ጽንዑ በተዋህዶ እምነት /፪/

መሠረት/፪/ ናትና ሕይወት /፪/

ርዕይክዋ

ርዕይክዋ ለቤተ ክርስቲያን አፍቀርክዋ ለቤተ ክርስቲያን /፪/

ዘኢትዮጵያ /፪/ ቤተ ክርስቲያን /፪/

አየኋት ቤተ ክርስቲያንን ወደድኳት ቤተ ክርስቲያንን /፪/

የኢትዮጵያ /፪/ ቤተ ክርስቲያን /፪/

መዝሙር በእንተ ሀገሪትነ ኢትዮጵያ

ኢትዮጲየ ታበጽህ እደዊሃ

ኢትዮጵያ ታበጽህ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር/2/
እንዘትብል አምላኪዬ/2/ ነጽረኒ ወአድኅነኒ
እምኃይለ ጸላኢ ወፀር

ትርጉም፣ በምሕረት ዓይን ተመልከተን ከጠላትኃይል አድነን እያለች ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ አግዚአብሔር ትዘረለች

ትሴብሃከ

ትሴብሃከ ኢትዮጵያ ወታሌእለከ ስመከ ውስተ ዓለም/፪/

በእንተ ማርያም ወላዲትከ ዕቀብ ብሔራ ለኢትዮጵያ/፪/

ትርጉም፡- ጌታ ሆይ ስምህን በዓለም ሁሉ እያነሳች የምታመሰግንህን ኢትዮጵያን ስለ እናትህ ስለ ማርያም ብለህ ጠብቃት፡፡

<u>አፍላገ ግዮን</u>

አፍላገ ግዮን ወጤግሮስ ይውኅዙ በወንጌል ሐዲስ/፪/

እም የማና ወእም ጸጋማ ኤፌሶን ወይን ኤፍራጥስ ኢትዮጵያ ሀገረ ክርስቶስ/፪/

ትርጉም፡- አራቱ አፍላጋት/ወንዞች/ ግዮን፣ ጤግሮስ ኤፌሶንና ኤፍራጥስ በ4ቱ መአዘንሽ የሚፈሱብሽ የ4ቱ ወንጌላውያን ቃል የሚነገርብሽ ኢትዮጵያ የእግዚአብሔር ሀገር ነሽ፡፡

<u>ሰላም ለኪ</u>

ሰላም ለኪ ኦ ዓባይ ሀገር ቅድስት ኢትዮጵያ ሀገረ እ፟ግ፟ዚአብሔር /2/

ስምድርኪ ምድረ ገነት እምአርባክቱ አፋላጋት ግዮን <u>አስተዩኪ</u> /2/

ግዮን ፈለገ ሕይወት ውሉድኪ /2/

ፈረዩ ፍሬ ሃይማኖት

ሰላም ለአንቺ ታላቅ ሀቶር ልዩም ሀቶር

ኢትዮጵያ የ፟እ፟ግ፟ዚአብሔር ሀቶር /2/

ምድርሽ የገነት ምድርን ከአራቱ

ወንዞች ዓባይ <u>አጠጣሽ</u> /2/ /2/

ዓባይ የሕይወት ምንጭ

ልጆችሽ አፈሩ የሃይማኖት ፍሬ

፟አ 2 ፣ 13

<u>ኢኮነ ነግደ</u>

ኢኮነ ነግደ ወፈላሴ ሀገሪቶሙ /2/

ሀገሪቶሙ ለቅዱሳን ኢትዮጵያ /4/

ትርጉም፡- ስ□ተኛ □እና መጻተኞች አይደለንም፡፡ ኢትዮጵያየቅዱሳን ሀገራቸው ናት፡፡